# ቲቢ (የሳንባ ነቀርሳ)

ቲቢ በባክቴሪያ ምክንያት የሚከሰት በሽታ ነው፡፡ በአብዛኛው ጊዜ ቲቢ በሳምባዎች ላይ የሚከሰት ሲሆን በሌሎች የሰውነት ክፍሎች ላይም ያጋጥማል (ለምሳሌ በአጥንቶች፣ የሊንፍ እባጮች ፣ ወይም በአዕምሮ)፡፡

- ቲቢ በህክምና የሚድን በሽታ ነው
- በኖርዌይ የቲቢ ምርመራ እና ህክምና በነጻ ይሰጣል

## በቲቢ እንዴት ሊያዙ ይችላሉ?

ቲቢ በሳንባው ውስጥ ያለበት ሰው በሚያስል ወይም በሚያስነጥስ ጊዜ ባክቴሪያው በአየር ውስጥ በአይን በማይታዩ ትናንሽ ጠብታዎች አማካኝነት ይሰራጫል፡፡ እነኝህን በአየር ላይ የተሰራጩ ጠብታዎች ወደ ውስጥ ያስገቡ ሰዎች በባክቴሪያው ይያዛሉ፡፡ የቲቢ ባክቴሪያ በቀላሉ አይሰራጭም ቅርበት ካለ ሰው ጋር፣ ለምሳሌ ከቤተሰብ አባል፣ የመያዙ አጋጣሚ ግን የተለመደ ነው፡፡

## የቲቢ ምልክቶች

የቲቢ የተለመዱ ምልክቶች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡-

- ከ 2 – 3 ሳምንታት ወይም ከዚያ በላይ የቆየ ሳል
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- የክብደት መቀነስ (በጣም ቀጭን መሆን)
- የአቅም መቀነስ እና ድካም ስሜት
- ለረዥም ጊዜ ትኩሳት ሲኖርዎ
- የሌሊት ላብ
- በጉሮሮ፣ በብብት እና ብሽሽት ውጫዊ ክፍል ላይ የሚታይ እብጠት ወይም መጓጎል



ከእነኝህ ምልክቶች አንዱ ወይም ከዛ በላይ የታየበት ማንኛውም ሰው ዶክተር ጋር ሄዶ መመርመር አለበት

## አስፈላጊ የቲቢ ምርመራዎች

ለተወሰኑ ቡድኖች የቲቢ ምርመራን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ የሚያጠቃልለው፣ ሎሎችንም ጨምሮ፣ በተለይ ቲቢ ከተስፋፋባቸው ሀገራት መጥተው በኖርዌይ ከሶስት ወራት በላይ የሚቆዩ ሰዎችን ነው፡፡ ምርመራው እድሜአቸው ከ 15 አመት በላይ ላሉ ሰዎች የደረት ራጅ እንዲሁም ከተቻለ የደም ናሙና መውሰድን ወይም የቆዳ ምርመራን ያጠቃልላል፡፡







የምርመራው አላማ ህመሙን ለመለየት እንዲሁም በተቻለ መጠን ቀደም ብሎ ችግሩን በማወቅ ህክምና ለመስጠትና እንዳይስፋፋ ለማድረግ ነው፡፡